Amharic

NEIGHBOURHOOD
Empowerment Team

# በስራ ቦታ ደህንነት አስፈላጊ ነው።





## ምንጭ

- **በኣቅራቢያህ የንግድ ማሻሻያ** በታዎች ማናገር።
- የኣከባቢህ ማ/ሰብ ሊግ ማነጋገር። ለማንኛዉም የማ/ሰብ ደህንነት የማ/ሰብ ሊግ በ **efcl.org.** ማግኘት ይቻላል።
- የኣከባቢህ **የጎረቤቶች ማበረታቻ ማህበር** መተዋወቅ ኣለብህ።
- **በኣከባቢህ የወንጀል ኣስተዳደር ማ/ሰብ** ማህበር ወይም **ቢትስ ቲም** መገናኘት።

ዳውን ታውን ኣከባቢ **780-421-2200**


ሰሜናዊ ምዕራብ ኣከባቢ፡ **780-423-4567**

ሰሜናዊ ምብራቅ ኣከባቢ፡**780-426-8100**

ደቢባዊ ምብራቅ ኣከባቢ፡ **780-426-8200**

ደቡባዊ ምዕራብ ኣከባቢ፡ **780-426-8300**

ምዕራብ ኣከባቢ፡ **780-426-8000**



# ስልጠና

**ሁሉም ደህንነት ለማረጋገጥ ሚና መጫወት ኣለበት። በስራ ቦታ የሚፈጠረው ኣደጋ በስልጠና ሊቀንስ ይችላል።**

የ **ኦኩፔሽን ሄልዝና ሴፍቲ ኣክት** በኣልበርታ ስራ ቦታ መከናወን ያለባቸው የጤናና የደህንነት ጥንቃቄ ይዘረዝራል።

የ ኦኩፔሽን ሄልዝና ሴፍቲ ስልክ ቁጥር በኢድመንተንና ኣከባቢዋ፥ 780-415-8690 ።

መስማት ለማይችሉ የኢድመንተን ስልክ ቁጥር፥ 780-427-9999

---

**የካናዳ ኣእምሮ ህመምተኞች ማህበር፦ በኢድመንተን ዙርያ**

**ለኣእምሮ ህመምተኛ የመጀመርያ እገዛ**

**main@cmha-edmonton.ab.ca ወይም በ 780-414-6300 መደወል**

ለኣእምሮ ህመምተኛ የመጀመርያ እገዛ ማድረግ ለሚያስተምሩ የካናዳ የኣእምሮ ህመምተኛ ኮሚሽን (MHCC) እንደ የካናዳ ኣእምሮ ህመምተኞች ማህበር ያሉ ድርጅቶች ስልጠና ይሰጣል።

በኢድመንተን ስልጠና የሚሰጡ ድርጅቶች ለማግኘት MHCC ጠይቅ።

**mhfa@mentalhealthcommission.ca ወይም ከክፍያ ነጻ መስመር: 1-866-989-3985 ተጠቀም።**

**ኦክፔሽናል ሄልዝና ደህንነት የካናዳ ማዕከል**

በጤና ደህንነት በኦንላይን፥ በዙምና በኣካል ስልጠና ይሰጣል።

**ccohs.ca/products/courses**
**clientservices@ccohs.ca ወይም በደንበኛ ኣገልግሎት 1-800-668-4284 ደውል።**

---

**ሴንት ጆን ኣምቡላንስ**

**stjohn.ab.ca**

የመጀመርያ ደረጃ ዕርዳታ ስልጠና

12304-118 Ave, Edmonton AB, T5L 5G8

**1-800-665-7114**

---

**ኣልበርታ ጌሚንግ፥ ሊኩየርና የካናቢስ ኮሚሽን**

**aglc.ca**

ስለ ጌሚንግ፥ ሊኩየርና የካናቢስ የሰራተኛ ስልጠና

50 Corriveau Avenue, St. Albert, AB T8N 3T5

ከክፍያ ነጻ: **1-800-272-8876**

---

**የኢድመንተን ፖሊስ ኣገልግሎት**

**edmontonpolice.ca**

ስልጠና የሚያካትተው፥ ኣከባቢን ያገናዘበ ወንጀል መከላከል፥ ከፖሊስ በመተባበርና የዜጎች ፖሊስ ት/ቤት

በተጨማሪም ወንጀል የመቀነስ ስልጠና ያበረታታል።

# በስራ ቦታ ደህንነት ኣስፈላጊ ነው።

**ይህ መረጃ ለንግድ ባለቤቶች እንዲሁም ለሰራተኞች በስራ ቦታ ወንጀልና እንግልት ለመቀነስ ያግዛል።የሚከተሉትን ኣንዱ ወይም ሌሎች ተጨማሪ የምክር ሃሳቦች በመጠቀም ይህ መረጃ በንግድ ቦታ የደህንነትና ጸጥታ ዕቅድ ለመንደፍ ያግዛል። ችግሮች ለመቅረፍ ስለሚያግዙ የሚከተሉትን የምክር ሃሳቦች እንድትጠቀሙ ተጋብዛችሃል።**



# በስራ ቦታ የመኪናህን ደህንነት ኣረጋግጥ

**ኣብዛኛው የተዘረፉ መኪኖች ሳይዘጉ በመተዋቸው ነው።**

- ሁሌ የመኪናህን በርና መስኮት ዝጋ፥። ቁልፍህን በራስህ ያዝ። ፈጽሞ የመኪና ሞተር እየሰራ ትተሀው ኣትሂድ።
- ውድ ዕቃዎች ማለትም የጋራጅ መክፈቻ፥ የመኪና ፋይል እና የኤለክትሪክ ገመዶች ከዕይታ ውጭ ኣስቀምጣቸው።
- ውድ የሆኑ ዕቃዎች ከመኪናህ ለመውሰድ የስቲከር ማስታወሻ ኣድርግ።ስቲከሮች በኣከባቢህ ፖሊስ ጣብያ ይገኛሉ።

**ምክር |** የመኪናህን ስርቆት ለማስቀረት የመሪ መቆለፍያ ተጠቀም።

- መኪናህ መብራት ባለበት ኣስቁም።
- በተቻለ መጠን በመኪና ማቆምያ ጥግ ኣድርጋት።
- ታርጋ በቀላሉ ስለሚሰረቅ በመኪናህ ታርጋ መኖሩ ኣረጋግጥ።
- ለመኪና ታርጋ የስርቆት መከላከያ መጋዝ ኣድርግበት።



# መብራት

**በደንብ መብራት ያላቸው ቦታዎች የስራ ቦታ ደህንነት እንዲኖር በማድረግ ወንጀል የመፈጠር ዕድል ኣነስተኛ ያደርጋል።**

## መደበኛ መብራት

- ሊድ ኣምፑል ተጠቀም። ትንሽ ሃይል በመጠቀም ለረጂም ጊዜ ኣገልግሎትና ጥሩ መብራት በመስጠት ደማቅ መብራት ይሰጣል።
- ሁሉም ኣምፖሎች መስራታቸውና ቆሻሻ ኣለመኖራቸው ኣረጋግጥ።
- ብስራ ቦታ የትና እንዴት መብራት መጠቀም እንዳለብህ ኣስብ። የተለያዩ መብራቶች በተፈለገ ቦታ ችግር እንዳይፈጠር ያደርጋሉ።
- ዕገዛ ካስፈለገህ በስራ ቦታ የትኛው የመብራት ዓይነት መጠቀም እንዳለብህ ለባለሞያ ኣማክር።

## ከበር ውጭ

- መብራት ከመሬት ከ9-18 ሜትር ከፍታ እንዲታይ ኣድርግ።
- የተለያዩ የውጭ መብራቶች እንዲኖሩ ኣድርግ።በመግብያ፥ በማስተላለፍያ፥ በጀርባ፥ በመኪና ማቆሚያ እና መዓዝኖች ኣከባቢ ሰዎች የሚደበቁበትና የሚሰበሰቡበት ቦታ።
- መብራቶች ከብልሽትና ከጥልፍልፍ ገመዶች(መሸፈኛ) ነጻ ኣድርጋቸው። ማለትም ወደሚፈለገው ቦታ መብራት እንዲያበራ ነው።
- መብራት በዛፎችና ቁጥቋጦዎች ኣለመጋረዳቸው እርግጠኛ ሁን።

## ውስጥ

- የስራ ቦታ በሚዘጋበት ጊዜ መብራቶች እንዲበሩ ካደረግክ ሰዎች በግልጽ እንዲታዩ ያግዛል።
- ትናንሽ ክፍሎችና የግምጃ ቤቶች በደንብ መብራት እንዲኖራቸው ኣድርግ።

**ምክር |** ዕይታ ለመጨመር ሊድ መብራት ከካሜራ ጋር ጥሩ ይሰራል።



# በስራ ቦታ ግልፍተኛ ሰው ማስተናገድ

**ሰራተኞች ግልፍተኛ ሰው እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ኣሰልጥናቸው።ግልፍተኛ ሰዎች ካጋጠሙ ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ በትክክል መፍትሄ ያገኛል።**

- ብር እንደሌለህ ንገራቸው።
- እየተከታተሉ እንዳልሆኑ በጥንቃቄ እያቸው።
- ለድንገተኛ ኣደጋ ባልሆነ መስመር 780-423-4567 ለፖሊስ ደውል።
- ለበለጠ ዕገዛ ሰውየው ወደ 211 እንዲደውል ንገረው።
- እገዛ ለማግኘት በ 211 ወደ ኣደጋ ክፍል 24/7 ደውል።

**ምክር |** ለሀይለኛ ሰዎች ብር ከመስጠት በስራ ውስጥ ብር በማሰባሰብ ለኣቹራቢያ የሚገኙ በጎ ኣድራጎት ድርጅቶች ኣበርክት።




## ዕይታ

**ሰዎች በሌሎች ሰዎች የሚታዩ ከሆኑ ወንጀል የመስራት ዕድላቸው ይቀንሳል።**

- የመስኮት መጋረጃ ካለው ቀን ላይ ክፍት ኣድርገው።
- ዕይታ የሚጋርዱ የዛፍ ቅርንጫፎች ከእግራቸው እስከ 6′ በመከርከምና ሌሎች ቁጥቋጦች ከ2′ ቁመት በታች ለማድረግ ዕይታ የሚጋርዱ ማስወገድ ይቻላል።
- የመስኮት ዕይታ ጥሩ መሆን ኣለበት። በመስኮት የማይታይ ቦታ ከ10% መብለጥ የለበትም።
- ኣጫጭር የመደርደርያ ክፍሎች ተጠቀም። ረጃጅም መደርደርያዎች ለሰራተኛ ዕይታ ስለሚያስቸግር ሌቦችና ወንጀለኞች መቆጣጠር ያስቸግረዋል።
- ዕይታ ግልጽ ለማድረግ የብረት ኣጥር ተጠቀም። ድፍን ኣጥር ሌባ እንዲደበቅ ያደርጋል።

**ምክር |** የስራ ቦታ ከውስጥ ኣራቱም ግድግዳዎች መታየታቸው ኣረጋግጥ። በመዓዝን ማየት ካልቻልክ ዕይታ የሚያግዙ ኣንጸባራቂ መስታዎቶችና ካሜራ ይደረግበት።



## የቤት ጀርባ ጸጥታ

**ከቤቱ ጀርባ ኣከባቢ ለወንጀል መፈጠር የታወቁ ዒላማዎች ናቸው። መብራት ካለውና ንጹ ከሆነ የወንጀል ቦታ የመሆን ዕድል ይቀንሳል።**

- በሮች ሁልጊዜ ዝግ ይሁኑ። እንዲሁም በማትጠቀምበት ጊዜ የቆሻሻ መጣያ ዝጋው።
- የተቃጠሉ የከተማ ኣምፖሎች ወድያውኑ በ 311 ኣሳውቅ።
- የእንቅስቃሴ ዳሳሽ መብራት በስራ ቦታ ጀርባ ኣድርግ። በጸሃይ ሃይል የሚሰሩ ኣሉ።
- ኣከባቢው ንጹና ከቆሻሻ ነጻ መሆን ኣለበት።
- በድርጅቱ ጀርባ ኣድራሻ ሁሌ ይኑሮው። ፖሊስና ሌሎች ሰዎች ተጠርጣሪ ሲያዩ በቀላሉ ኣድራሻ ለማየት ያግዛል።

**ምክር |** ሰዎች ወደ ቦታው ጀርባ መጥቶው እንዲጫወቱና እንዲዝናኑ የድርጅቱ ጀርባ ግድግዳው ላይ ጥሩ ስዕሎች ወይም የስነ-ጥበብ ስራ ኣንጠልጥልበት።



# ኣላርምና የቪድዮ ክትትል

**የደህንነት ካሜራ መግጠም ለኣደጋዎች ምላሽ ለመስጠት ስለሚያግዝ ወንጀልና መሰል ችግሮችን ያስቀራል።**

- ከስራ ቦታ ሰራተኛ ሲለቅ ኣላርም ኮድ ቀይር።
- ሪፖርት ማድረግ እንዲችሉ ሰራተኞችን የቪድዮ ክትትል እንዴት እንደሚያደርጉ ኣሰልጥናቸው።
- የደህንነት ኣላርም ወይም የቪድዮ ክትትል ለመዘርጋት ከኣቅራብያህ መግዛት ትችላለህ ወይም ለባለሞያ ኣማክር።
- ጭጋጋማ ምስል እንዳይኖር የደህንነት ካሜራ በየወሩ ወልውላቸው።
- **የካናድያን ኣላርም ደህንነት(CANASA)** እና በላቦራቶሪ ካናዳ(ULC) የተረጋገጠ ኣላርም ካላቸው ድርጅቶች ግዛ።
- የኣላርም ዝርጋታ ከማድረግህ በፊት የኣላርም የመጠቀም ፈቃድ እንደሚያስፈልግ ታውቃለህ? ለበለጠ መረጃ **edmontonpolice.ca/alarmbylawprogram** ይጎብኙ።
- የተሳሳተ ኣላርም ወደ ፖሊስ ሪፖርት ከማድረግህ በፊት ሰራተኞች የኣላርም ኮድን ወደ ኣላርም ድርጅት እንዴት መደወል እንዳለባቸው ኣሰልጥናቸው።
- ሰራተኞቹ ውስጥ እያሉ ከኣላርም ድርጅት ኣላርም ጠፍቶዋል ብሎ ከተናገረ ወደ ፖሊስ የሚደረገው ጥሪ ማቅረባቸው እርግጠኛ መሆን ኣለብህ።

**ምክር |** የደህንነት ዝርጋታ ለማድረግ ቅናሽ ካለ የራስህ ኢንሹራንስ ድርጅት ጠይቅ።system.

**ምክር |** የኢድመንተን ፖሊስ ኣገልግሎት የቪድዮ ሪኮርድ ለ30 ቀናት እንዲያዝ ይመክራል።




# ክሳራን መከላከል

**ገቢህን ለማሳሻልና ኣላስፈላጊ ክሳራ ለማስቀረት የሚከተሉትን ኣድርግ።**

- ጸረ-ስርቆት ምልክቶች ኣድርግ።
- በዝርዝር ሁልጊዜ ተቆጣጠር።
- በሽፍት መቀያየርያ ጊዜ ገንዘብ ሲቆጠር ትላልቅ ሂሳቦች የያዙ መዝገቦች ከገንዘብ ያዥ ቦታ ኣከባቢ ኣርቅ።ብር የሚቀመጥበት ካዝና ሁሌ ከተፈለገው መጠን በላይ እንዳይሆን ኣረጋግጥ።
- ደህንነቱ የተጠበቀ ስራ የሚሰራ ሰራተኛ መድብ።ስራ በሚበዛበት ጊዜ ተጨማሪ ሰራተኞች መድብ።
- ውድ ዕቃዎች ቆልፋቸው ወይም ከመስኮት ራቅ ብሎ ሰራተኛ በሚያይበት ቦታ ይቀመጥ።
- በደቢትና ክረዲት የሚገዙ ዕቃዎች ኣትለያይ። በተጨማሪም የተለያዩ ግዢ በሚያደርጉ ሰዎች ትኩረት ኣድርግ።

**ምክር | የግድግዳ ሰዓት**
እይ።በEPS ፖሊስ የስርቆት መከላከል መርሃግብር ለንግድ ባለቤቶችና ሰራተኞች፣ የነሱ ንብረትና ደንበኞች ደህንነት ለመጠበቅ የተዘጋጀ ነው።



## ማስዋጥ

**በውስጥም በውጭም ንጹና ጥሩ ጥገና የሚደረግለት የስራ ቦታ ወንጀልን ለመከላከል ምቹ ቦታ ይፈጥራል። ቆሻሻ ፥ ግራፊቲና የተሰባበሩ መስኮቶች ካሉ ትኩረት ስጥ።**

ቆሻሻ ለመቀነስና ግራፊቲ ለመከላከል የሚከተለው ድህረገጽ ይጎብኙ።
**edmonton.ca/capitalcitycleanup ወይም 311 ደውል።**

- ቤትህ የግራፊቲ ታሪክ ካለህ የማ/ሰብ ግድግዳ ተጠቀም።
- ለሰዎች ዋና መግብያ ለመለየትና የሰዎች ያለምክንያት መመላለስ ለመቀነስ ማራኪ የመሬት ኣቀማመጥና ረጃጅም የማስታወቅያ ተከላ ተጠቀም።
- ያገለገለ መርፌ በቤትህ ካገኘህ" **ጥቅም ላይ የዋለ ማስወገጃ ዘዴ ተጠቀም"**
- በስራ ቦታ ፊትለፊት የቆሻሻ መጣያ የሚያሳይ ማስታወቅያ ሰዎች በሚዝናኑበት ቦታ ኣድርግ።

የስራ ቦታ ማሻሻያ እይ ወይም የሚከተሉትን መስፈርቶች የምታሟላ ከሆንክ 311 ደውል።

- የፊት ገጽታ የማሻሻያ ማበረታቻ መርሃግብር **edmonton.ca/facadeprogram**
- ማሻሻያ ማበረታቻ መርሃ ግብር **edmonton.ca/developmentincentiveprogram**

**ምክር |** ስራ ቦታ ለማስዋብ ኣበባ መትከልና የመሬት ኣቀማመጥ ማስተካከል ትንሹ ወጪ ነው።



## ኣከባቢህ በንቃት መከታተል

**ሰዎች ወደ ስራ ቦታ ሲመጡ ክትትል ማድረግና ለምን ዓላማ እንደመጡ ማወቅ።**

- በኣደጋ ጊዜ ሰራተኞች ምን እንደተፈጠረና በድንገተኛ ያልሆነ መስመር **780-423-4567** ወይም በመንጀል ድጋፍ መስመር : **1-800-222-8477** ለፖሊስ የፈጸመውን ሰው በደንብ ገለጻ እንዲያደርጉ ማሰልጠን።
- በስራ ቦታ የመክፈቻና የመዝግያ ሰዓት፥ የደህንነት ኣጠባበቅ ዘዴ ፥ የሰራተኛ መቀያየርያ ሰዓትና ህንጻው ለረጂም ግዜ ማየት ወይም ያለምክንያት እዛው ኣከባቢ መቅለስለስ የሚያበዙ ሰዎች ላይ ትኩረት ኣድርግ።

**ምክር |** **ውክልና** ይኑርህ።የንግድ ባለቤቶች ለፖሊስ ኣባላት እንድያጣሩላቸው ይወክሉዋቸው።

- ኮፍያና መነጽር የሚያደርጉ ሰዎች በተጨማሪም ትልቅ ሻንጣ ይዞው ወደ ስራ ቦታ የሚገቡ ሰዎች ተከታተላቸው።
- ለረጂም ግዜ በመኪና ማቆምያ ቦታ የሚቀመጡ ሰዎች ተከታተላቸው።
- ለማድረግ ኣመቺ ከሆነ የተጠርጣሪው መኪና ታርጋ መዝግብ።
- ኣደጋ ሲያጋጥም ሰራተኞች የኣደጋ ግዜ መውጪያ በርና ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ ማረጋገጥ ኣለብህ።



# ኣጠቃላይ ጥገና

## ለቆሻሻና ለተሰበሩ መስኮቶች ትኩረት ስጥ።

- የተሰበሩ መስኮቶች ጥገና ኣድርግላቸው።
- የእንስሶችና የሰዎች ቆሻሻ ኣንሳ። በጥንቃቄ እንዴት ማስወገድ እንዳለብህ ለማወቅ 311 ደውል።
- የህዝብ መጸዳጃ በማሳየት ባንተ ቦታ የሚጸዳዱ ሰዎች ደንበኞች ብቻ መሆናቸው ንገራቸው።በኣቅራብያ የህዝብ መጸዳጃ ለማግኘት Open Data ተጠቀም።
- የግል መኪና ማቆምያ መሆኑ ለማሳየት ግልጽ የሆነ ምልክት ኣድርግ። ለበለጠ መረጃ የከተማ ህገ ደንብ ማየት ይቻላል። edmonton.ca/parkingonprivateproperty.
- ኣድራሻህ ከህንጻው ፊትና ኋላ በትክክል መቀመጡ ኣረጋግጥ።
- ለሁሉም ሰዎች እንቅስቃሴ ደህንነት የቤትህ መንገድ መተላለፍያ በረዶ ካለው ወድያውኑ ጥረገው። ይህን ግዴታ ላልተወጣ የቤት ባለቤት ቅጣት ይጠብቀዋል። ለበለጠ መረጃ edmonton.ca/wintersidewalks ይጎብኙ።

## ቆሻሻ ወይም ጽሁፍ የተቀመጠበት ቦታ እንዴት ማጽዳት ይቻላል።

- **መዝግበው፥**ፎቶ በማንሳት ቦታና ግዜ መመዝገብ።
- **ሪፖርት ኣድርግ፥** ወደ 311 በመደወል ለ ኢድመንተን ፖሊስ ኣገልግሎት (EPS) ኦንላይን ሪፖርት ኣድርግ።
- **ኣስወግደው፥** የኢድመንተን ከተማ ለቤት ባለቤቶች በየወቅቱ ኣንዴ ቆሻሻ በባለ ሞያተኞች እንዲነሳ እስከ $750 ያግዛል።



## ንብረትህ ቆልፈው

**የስራ ቦታ መቆለፍ ሌላ ሰው ያለፈቃድ ወደ ቦታህ የመግባት ዕድል ይቀንሳል።**

- ወደ ውጭ የሚከፈቱ በሮች የማይነቀል ማንጠልጠልያ ፒን መኖራቸው ኣረጋግጥ። በራሱ የሚዘጋ በር ረጇም መቆለፍያ ማድረግህ ኣትርሳ።
- መቆለፍያ በሃይል በመጫን በፍጹም ክፍት ኣለመተው።
- የኋላና የጎን መግብያ መቆለፋቸው ኣረጋግጥ። ከተቻለ ሰራተኞች በዋናው በር እንዲወጡ ኣድርግ።
- ሰራተኞች ወደ ቤታቸው ሲሄዱ የመውጭያ ግዜ ፎርማ ወረቀት በማዘጋጀት ቁልፎች እንድያስረክቡ ማድረግ።
- በስራ መውጭያ ሰዓት በሮችና መስኮቶች በትክክል መዘጋታቸው ኣረጋግጥ።